የሚኖሶታ የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር

# የንግድ ስራ አገልግሎት

First National Bank Building,
332 Minnesota Street, Suite N201
Saint Paul, MN 55101
business.services@state.mn.us
651-296-2803

# ጠቃሚ የባለቤትነት መረጃ ሪፖርት የማድረግ አዲስ የማእከላይ መንግስት መስፈርት

ከጥር (January) 1 ቀን 2024 ጀምሮ በአሜሪካ ውስጥ ያሉ አያሌ ኩባንያዎች፤ ስለ **ባለቤቶቻቸው** ለ አሜሪካ የገንዘብ ሚኒስቴር ወንጀል ክፍል (United States Department of the Treasury's Financial Crimes Enforcements Network) (FinCEN) መረጃ መስጠት አለባቸው- ባለቤቶች ሲባል ኩባንያው የራሳቸው የሆኑ ወይም ኩባንያውን የሚቆጣጠሩ ሰዎች ማለት ነው።  ይህ ዓይነቱ መረጃ የመስጠት ተግባር የሚደረገው **በነጻ** ነው። አንላይን ውስጥ ወደ www.fincen.com/boi (ኮንትሮል+ በመጫን ወደ መገናኛው ያመራሉ) በመግባት ሊደረግ ይችላል።

## ሪፖርት ማድረግ ያስፈልገኛልን ?

**በሚኖሶታ ውስጥ ያሉት ንግድ ቤቶች አነስተኛ ንግድ ቤቶች ስለሆኑ ሪፖርት ማድረግ አለባቸው።**

ድርጅትዎ ስለባለቤቶቹ ሪፖርት ማድረግ ያለበት ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የሚመለከተው ሲሆን ነው፡

1. ኮርፖሬሽን፣ ሃላፊነቱ የተወሰነ ድርጅት(ኤል-ኤል-ሲ LLC)፣ወይም በአሜሪካን አገር ውስጥ፤ በህንድ ጎሳ ህግ መሰረት በአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር ወይም በሌላ ህጋዊ ተቋም ውስጥ ማመልከቻ በማስገባት የተመሰረተ ሲሆን፤
2. በዚህ በተደረገው ምዝገባ፤ አንድ የውጭ አገር ድርጅት በማንኛውም የአሜርካን ክፍለ ሃገር ወይም የህንድ ጎሳዎች በሚኖሩበት ክልል  የንግድ ስራ ለማካሄድ የተመዘገበ

**23 ዓይነት የንግድ ስራዎች ከዚህ መረጃ ሪፖርት** የማድረግ ሃላፊነት ነጻ ናቸው። የፊንሴን (FinCen) **ትናንሽ ንግዶች ሊይሟሏቸው የሚገቡ ነገሮች መመርያ (Small Entity Compliance Guide)፡** ንግዶ እነዚህ ነጻ ከሚያስደርጎ ነጥቦች ውስጥ አንዱም ቢሆን ይመለከተዋልን የሚል ጥያቄ መልስ ያዘለ ነው። ስለዚህ የእርሶ ድርጅት ነጻ ነው አይደለም ለሚለው ጥያቄ መልስ ለማግኘት **www.fincen.gov/boi** ዐበመግባት ይጎብኙ።

*ትናንሽ ንግዶች ሊይሟሏቸው የሚገቡ ነገሮች መመርያ*

## እንዴትና መቼ ነው ሪፖርት የሚደረገው?

ጠቃሚ የሆነ የባለቤትነት መረጃ ሪፖርት ማደረግ ያለባቸው ድርጅቶች ሪፖርት ማድረግ ያለባቸው በኤሌክትሪካዊ መንገድ በ ፊንሴን ዌብሳይት www.fincen.gov/boi አማካኝነት ነው።

FinCEN ከ ጥር (January) 1 ቀን  2024 ጀምሮ ሪፖርቶችን መቀበል ጀምሯል።

- ድርጅትዎ የተመሰረተው ወይም የተመዘገበው ከጥር (January) 1 ቀን  2024 በፊት ከሆነ፤ ጠቃሚ የባለቤትነት መረጃን ሪፖርት ለማድረግ እስከ ከጥር (January) 1 ቀን  2025 ግዜ አሎት።
- ድርጅትዎ የተመሰረተው ወይም የተመዘገበው ጥር (January) 1 ቀን  2024 ወይም ከዛ በኋላ ከሆነ፡ ድርጅትዎ ሲመሰረት ወይም ሲመዝገብ ባሉት 90 ቀናት ውስጥ መረጃውን ሪፖርት ማደረግ አለቦት፡ የሪፖርት ማቅረብ ግዜ ደግሞ 30 ቀናት ነው።
- ፊንሴን (Fincen) በኩል በተሰጠው ጠቃሚ የባለቤትነት መረጃ (BOI) እርማት ወይም ጭማሪ ቢያስፈልግ እርማቱ በ 90 ቀናት ውስጥ መሰጠት አለበት።

ለተጨማሪ መረጃ www.fincen.gov/boi ይጎብኙ።